Australian Government

Department of Immigration and Multicultural and Indigenous Affairs

# ቪዛና ዜግነት ለሚጠይቁ አመልካቾች ስለ ዲኤንኤ (DNA) ማለትም ስለደም ምርመራ የቀረበ መግለጫ

Form 1259i AMH

## ዲኤንኤ (DNA)

ዲኤንኤ (ዲኦክሲራይቦኒዩክሊክ አሲድ) ማለት በእያንዳንዱ የሰውነት ሴል (ሕዋስ) ውስጥ የሚገኝ የጀኔቲክ ማቴሪያል ነው። ለምሳሌ፡ በደም፤ በምራቅ፤ በቆዳና በፀጉር ውስጥ ይገኛል። ሁሉም ሰው ዲኤንኤ አለው። አንድ ሰው የራሱ የሆነ ዲኤንኤ ከቤተሰቦቹ ይወርሳል። ለዚህም ነው የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ የሆነ ዲኤንኤ የሚኖራቸው።

## የዲኤንኤ ምርመራ

የዲኤንኤ ምርመራ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ሰዎች የጀኔቲክ ማቴሪያል ወስዶ በማነጻጸር በመካከላቸው የስጋ ዝምድና እንዳለ ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው። ለምርመራ የሚሆነው የጀኔቲክ ማቴሪያል የሚወሰደው ከአፍ ውስጥ በጥጥ ተጠርጎ ወይም ከደም ናሙና ነው።

## አንዳንድ አመልካቾች ለምንድነው የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ የሚጠየቀው

የኢሚግረሽንና የሕብረባሕል እና የኢንዲጂነስ ጉዳዮች መምሪያ (ከአሁን በኋላ መምሪያ ተብሎ ይጠቀሳል) የስጋ ዝምድና አለን የሚሉ ሰዎች እውነተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት አንዱ ዘዴ የዲኤንኤ ምርመራ ነው። እንደተለመደው ሌሎች መረጃዎችም ለምሳሌ፤ የልደት ሰርተፊኬት ወይም የቤተሰብ መዝገቦች ይታያሉ። ይሁን እንጂ የዲኤንኤ ምርመራ የሚደረገው የስጋ ዝምድና አለን የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት ሰነድ በቂ ካልሆነና ወይም ምንም ማስረጃ ማቅረብ ካልቻሉ  የሚደረግ ምርመራ ነው።

ባለጉዳዮች የስጋ ዝምድና እንዳላቸው ለማሳየት ያቀረቡትን ማስረጃ መምሪያው ካላመነበት፡ እውነቱን ለማረጋገጥ ሲል የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደረጉ ሊጠይቅ ይችላል።

ቪዛ ወይም በመዋለድ የአውስትራሊያ ዜግነት ለማግኘት የስጋ ዝምድና እንዳለ ለማሳየት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ። የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በትውልድ ዝምድና እንዳለ የረጋግጣል፤ ለምሳሌ፤ በወላጆችና በልጆች ወይም በወንድሞችና በእህቶች መካከል ያለውን የስጋ ዝምድና ለማረጋገጥ ይቻላል።

## የዲኤንኤ ምርመራ የግዴታ የሚደረግ አይደለም

የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት ለምን ተግባር እንደሚውል ካወቁ አላደርግም ማለት ይችላሉ። በዚህም አይገደዱም።

የዲኤንኤ ምርመራ ማድረግ አለብዎት ብሎ የሚያስገድድ ሕግ የለም። የዲኤንኤ ምርመራ ተጨማሪ የሆነ መረጃ ለማግኘት ነው እንጂ ግዴታ አይደለም፤ የልደት ሰርተፊኬት ካልኖርዎት ሌላውና አንዱ አማራጭ ይሄው ነው። የዲኤንኤ ምርመራ ለማድረግ ሲወስኑ የሚፈልገውን ማሟላት እንዲችሉ ምን ማድረግ እንደሚገባዎት መምሪያው መመሪያ ይሰጥዎታል። መምሪያው ከሚጠቁማቸው ላቦራተሪዎች ውጪ የሚመጡ የምርመራ ውጤቶች ጠቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል።

የዲኤንኤ ምርመራ አላደርግም ብለው ከወሰኑ፡  ባቀረቡት የቪዛ ወይም በመዋለድ የአውስትራሊያ ዜግነት ማመልከቻ ላይ መምሪያው የሚወሰደው ውሳኔ በሰጡት ሌሎች መረጃዎች ላይ ብቻ ተመርኩዞ  ይሆናል።

## ለዲኤንኤ ምርመራ የሚደረግ ወጪ

የሰደተኛ ቪዛ ወይም በመዋለድ የአውስትራሊያ ዜግነት የሚጠይቁ አመልካቾች ሁሉ ለዲኤንኤ ምርመራ የሚፈልገውን ወጪ ሁሉ መክፈል ያለባቸው እነርሱ ናቸው።

የሬፊውጂ ቪዛ አመልከቾች ለዲኤንኤ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ መምሪያው ይሸፍናል። ይሁን እንጂ የሰብአዊ ፕሮግራም (ስፔሻል ሁማኒተሪያን ፕሮግራም) አመልካቾች የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ ከተጠየቁ የሚፈለገውን ወጪ ሁሉ መክፈል ያለባቸው እነርሱ ናቸው።

## ምክክር

የዲኤንኤ ምርመራ ለመውሰድ ከመወሰኖ በፊት ከጤና ባለሙያዎች ወይም ከዶክተሮች ጋር ምክክር (ካውንስሊግ) ለማድረግ ይችላሉ። የዲኤንኤ ምርመራ ውጤቱ ከታወቀ በኋላም እንከዋን ከጤና ባለሙያዎች ጋር መመካከር ይችላሉ።

**ማስታወሻ፡** ለመመካከር (ለካውንስሊግ) የሚወጣውን ወጪ የሚከፍሉት እርሶኖት።

## የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት የሚያሳየው

የወላጅና የልጅ ዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በመከከላቸው የስጋ ዝምድና እንዳለ ነው የሚያሳየው።

የተገኘው ውጤት ብዙውን ጊዜ እንደሚያሳየው አመልካቾች ያቀረቡት የስጋ ዝምድና ግንኙነት እውነት እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል።

የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሌሎች የቤተሰብ አባሎች ያላቸውን የስጋ ዝምድና በማያሻማ መንገድ ማሳየት አይችል ይሆናል። ውጤቱ ግልጽ ካልሆነ ላቦራተሪው ማብራሪያ ይሰጥበታል።

## የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት የሚውለው ለምን ተግባር ነው

ለመምሪያው የሚሰጠው የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት የሚውለው በቀጥታ ለኢሚግሬሽን ጉዳይ ብቻ ይሆናል።

## የግል ጉዳይንና ሚስጥርን መጠበቅ በተመለከተ

መምሪያው የግል ሚስጠርን አስመለከቶ በ1988 (እ.ኤ.አ.) በወጣው የሕግ አንቀጽ መሰረት የተገደበ ነው።

የዲኤንኤ ምርመራ ላቦራተሪዎች ለመምሪያውም ሆነ እርስዎን ስፖንሰር ላደረገው ሰው ወይም ድርጅት ውጤቱን ከማሳወቃቸው በፊት ከእርሶ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ይገባቸዋል እንጂ ለማንም አሳልፈው መስጠት አይችሉም።

የዲኤንኤ ምርመራ ውጤትን በግል ሚስጥር ጠብቆ መያዝን በተመለከተ ምርመራውን የሚያደርገው ላቦራተሪ ተጨማሪ መረጃ ይሰጥዎታል።

## ቤተሙከራ (ላቦራተሪዎች)

መምሪያው የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ ሲጠይቅዎት ለኢሚግሬሽን ጉዳይ አመቺ ናቸው ብሎ ወደሚያምንባቸውና ቅድመ ዝግጅት ወደአደረገባቸው ላቦራተሪዎች ብቻ ይልከዎታል። የነዚህ ላቦራተሪዎች ዝርዝር መምሪያው ለባለጉዳዮች በሚልከው ደብዳቤ ውስጥ ሰፍሯል።

## የዲኤንኤ ምርመራ ሂደት

የዲኤንኤ ምርመራ ሂደት የሚከተሉትን ደረጃዎች ያካትታል።

1. የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ መምሪያው ደብዳቤ ይልክሎታል። በደብዳቤው ውስጥም ሰለ ዲኤንኤ ምርመራ መረጃዎች፤ የምርመራ ሂደትንና የዲኤንኤ ምርመራ ላቦራተሪዎችን ዝርዝር ይይዛል።

2. በዲኤንኤ ምርመራው ለመቀጠል መወሰን ይኖርብዎታል። ከፈለጉም ከጤና ባለሙያዎች ወይም ከዶክተሮች ጋር ምክክር ማድረግ ይችላሉ።

   የዲኤንኤ ምርመራ ላለማድረግ ከወሰኑ፡ ያቀረቡት የቪዛ ወይም በመዋለድ የአውስትራሊያ ዜግነት ማመልከቻ ላይ መምሪያው የሚወሰደው ውሳኔ በወቅቱ በቀረቡለት መረጃዎች ላይ ብቻ ተመርኩዞ ይሆናል።

በሚቀጥለ ገጽ ይመልከቱ ▶

© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2005

3. በዲኤንኤ ምርመራው ለመቀጠል ከወሰኑ፡ የዲኤንኤ ምርመራ ከሚያደርገው ላቦራተሪ ጋር ተገናኝተው ቀጠሮ መያዝ አለብዎት። ክፍያውንም በተመለከተ ከላቦራተሪው ጋር መጨረስ አለብዎት።

4. ከዚያም በኋላ እርሶና ሌሎቹ አመልካቾች ናሙና እንድትሰጡ ላቦራተሪው ጥሪ ይልካል። ናሙና ብዙውን ጊዜ የሚወሰደው ከአፍ ውስጥ በጥጥ ተጠርጎ ወይም ከደም ጠብታ ነው።

   በውጪ አገር የሚገኙት ባለጉዳይ ተመርማሪዎች ሁሉ የምርመራ ናሙና ሲሰጡ የመምሪያው ተወካይ በታዛቢነት የግድ መገኘት ይኖርበታል። በአውስትራሊያ ውስጥም ቢሆን ናሙና ሲወሰድ አልፎ አልፎ ታዛቢ ይገኛል።

   መምሪያው የሚፈልገውን የማያሟሉ የዲኤንኤ ምርመራዎች ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል። (በአውስትራሊያ ውስጥ በሕግ የታወቁ የዲኤንኤ ምርመራ ውጤቶች ተቀባይነት ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል።)

5. የምርመራ ውጤቱ በቀጥታ ወደ መምሪያው እንዲላክ መስማማትዎን ለመግለጽ በፊርማ እንዲያረጋግጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። የዲኤንኤ ምርመራ ውጤቱ ለእርሶም ሆነ ለመምሪያው ይላካል።

   የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት ብዙውን ጊዜ የሚታወቀው ላቦራተሪው ናሙና ከወሰደ ከ14 ቀን በኋላ ነው።

   **ማስታወሻ፡** ለረፊውጂ አመልካቾች የዲኤንኤ ምርመራ ሂደቱ ለየት ያለ ነው። ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ሁሉ መምሪያው ያሳውቃል።

## ይህን መረጃ በተለያዩ ቋንቋዎች ያገኙታል

ይህ መረጃ በተጨማሪም በሚከተሉት ቋንቋዎች ተተርጉመው ይገኛሉ

- አማርኛ፤
- አርብኛ፤
- ዳሪ፤
- ፈረንሳይኛ፤
- ማንደሪን፤
- ሶማሊኛ፤
- ታገሎግ፤
- ቬትናምኛ።

## ስለ ዲኤንኤ ምርመራ ተጨማሪ መረጃዎች ከፈለጉ

እርሶም ሆኑ ዘመድዎ የዲኤንኤ ምርመራ ከተጠየቃቸሁና ያልገባዎትን ነገር ለማወቅ፤ ወይም ስለ ዲኤንኤ ምርመራ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ከፈለጉ ምርመራ እንዲያደርጉ የጠየቅዎትን የመምሪያውን ክፍል ያነጋግሩ ወይም የመምሪያውን ድረ-ገጽ **www.immi.gov.au** ይጎብኙ።

| | |
|---|---|
| *የድረ-ገጽ መግቢያ* | **www.immi.gov.au** |
| *አጠቃላይ የመረጃ መስመር* | በስልክ ቁ. **131 881** በአውስትራሊያ በስራ ሰዓት በመደወል ኦፕሬተር ያነጋግሩ ሉከዚ ሰዓት ውጪ ከሆነ የተቀረጸውን ድምጽ በማዳመጥ መረጃ ያገኛሉ። ከአውስትራሊያ ውጪ ከሆኑ በአቅራቢያዎት የሚገኘውን የአውስትራሊያን መልከተኛ ጽ/ቤት ያነጋግሩ። |


© COMMONWEALTH OF AUSTRALIA, 2005